በአሏህ ሰም እጅግ በጣም አዛኝ እጅግ በጣም ሩህሩህ

ከኡመር ቢን ኸጣብ እዳስተላለፉት ሙስሊም በዘገቡት ኡመር ቢን ኽጣብ እንዲህ አሉ ከመልክተኛው ጋራ ተቀምጠን ነበር በዚያን ጊዜ አንድ ልጅ ብቅ አለ ልጁ የለበሰው ልብስ እጅግ የነጣ ጸጉሩ እጅግ የጠቆረ ነበር። የመንገደኛ ምልክት አይታይበትም ከኛ መካከል የሚያውቀው አልነበረም ከዚያም ጉልበቱን ከመልክተኛው ጉልበት ጋር አስጠጋና መዳፎቹን በታፋዎቹ ላይ አድርጉ ‹‹ ሙሀመድ ሆይ እስኪ ስለእስልምና ንገረኝ›› ሲል ጠየቀ የአሏህ መልእተኛም እዲህ አሉ‹‹ እስልምና ማለት ከአላህ ሌላ በእውነት የሚገዙት አምላ አለመኖሩን እና ሙሀመድም የአሏህ መልእክተኛ መሆናቸውን መስክረህ በተጓዳኝም ሶላትን መስገድ፣ ዘካን በማውጣት፣የረመዷን ወር በመፆም ቻይ ከሆንክም ስነ-ስርአት መፈፀም ነው›› ሲሉ መለሱ ልጁም የመልእክተኛውን መልስ በሰማ ጊዜ‹‹ እውነት ተናገርክ›› ሲል አረጋገጠላቸው ኡመር እንዲህ አሉ‹‹ እጅግ ተገረምን ልጁ ይጠይቃል ሆላ እውነት ብለሀል ይላል›› ‹‹ እስኪ ስለ ኢማን ንገረኝ አላቸው›› መልክኛው እዲህ አሉ በአሏህ፤ በመላእክቶች፤በመፃህፍቶች፤ በመልእክተኞች፤ በመጨረሻዋ ቀን እዲሁም መልካም ሆነ መጥፎ ነገር የሚከሰተው በአሏህ ውሳኔ መሆኑን ልታምን ነው›› ልጁም ‹‹ እውነት ተናገርክ ሲል አረጋገጠላቸው›› ከዛም ‹‹ ስለ ኢህሳን ንገረኝ ›› አላቸው ‹‹መልተኛም ኢህሳን ማለት አሏህን እንደምታየው ሆነህ መገዛት ሲሆን ባታየው እንኳን እንንደሚያህ አውቀህ መገዛት ነው›› ልጁ ጥያቄውን ጠየቀ ‹‹ እስኪ ስለምፅአት ቀን ንገረኝ ›› መልእክተኛው እንዲህ አሉ ‹‹ ተጠያቂው ስለጉዳዮ ከጠያቂው የበለጠ አያውቅም›› እሲ ስለምክቶቿ ንግረኝ አላቸው ‹‹ እሳቸውም ባሪያ አሳዳሪዋን መውለዷ እዲሁም የታረዙ ጫማ የሌላቸው ድሀ እና ፍየል ጠባቂ የነበሩ ሰዎች በህንፃ እርዝማ ሲፎካሩ ታያለህ ሲሉ ነገሩት ›› ከዛ ልጁ ተነስቶ ሄደ።

ከሶስት ቀን በኋላ መልክተኛው ለኡመር እንዲህ አሉ ፡- ‹‹ ኡመር ወይ ጠያቂው ማ እነደሆነ አወቅህ›› ኡመርም‹‹ አሏህና መልእክተኛው ይወቁ አሉ ›› ‹‹ እሱ ጅሪል ነው የመጣውም ዲናችሁን ሊያስተምራችሁ ነው አሉ››

አቂዳህ

ክፍል፡- በማንኛውም ለጠጠያቂነት የደረሰ ሁሉ እስልምናን ሀይማኖት አድርጎ ሊይዝ ይገደዳ በዛም ላይ ሊፀና ይገባል። በኢስላማዊ ህግጋቱ (ሸሪአው) ሊሰራም ተገዷል። ይህመ የሚሆነው ግዴታ የሆኑ ነገራቶችን በመፈፀምና ሀጢያት የሆኑ ነገራቶችን በመከልከል ነው።

ክፍል፡- ‹‹ አሸሀዱ አን ላኢላ ኢለሏህ ማለት›› አውቃለሁ በልቤም አምናለሁ በአንደበቴም እመሰክራለሁ ።

ከአሏህ በስተቀር ነገራቶችን ግኡዝ አካላትንም ሆነ የአካላቶችን ድርጊቶች ካለመኖር ወደ መኖር የሚያስገባ ወይንም የሚፈጥር የለም ማለት ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ አምልኮ (የመጨረሻ የሆነ ፍርሀትና መተናነስ) የሚገባው የለም ማለት ነው።

አሸሀዱ አን ሙሀመደን ረሱለሏህ ማለት አውቃለሁ በልቤም አምናለሁ በአንደበቴም እመሰክራለሁ የቁርየሽ ጎሳ አባል የሆኑት ሙሀመድ ቢን አብዲላህ ቢን አብዲልሙጦሊብ የአሏህ ባሪያ የአሏህ መልእክተኛ ናቸው። የተላኩትም ለአለማት ማለትም ለሰውልጅ እና ለአጋንንቶች የተላኩ መሆናቸውን ከማመን ጋር።

ክፍል፡- በአሏህ ማመን ሲባ የአሏህ እውነታ የፍጡሯችን እደማይመስልና ሙሉእ በሆኑ ና በሱ ላይ በሚያች ባህሪ እንደሚገለፅ ከማመን ጋር ነው ከነዚህ ሙሉ ከሆኑ ባሪቶች መካከል፡

1 አል ውጁድ ፡- አሏህ ያለ ነው ለመኖሩ ጥርጥር የለውም

2 አል ወህደኒያ ፡- በጌትነቱ አጋር የሌለው እሱ ብቸኛ ነው አጋር የለውም

3 አል ቂደም ፡- አሏህ ለመኖሩ መጀመሪያ የለውም

4 አል በቃእ ፡- አሏህ ዘላለማዊና የመይጠፋ ጌታ ነው

5 **አልቂያሙ ቢነፍሲሂ ፡-** ከሱ ውጪ ካሉ ነገራቶች በጭራሽ አይከጅልም

6. አልቁድራ ፡- አሏ በሁሉም ነገር ቻይ ነው

7. **አል ኢራዳ** ፡- አሏህ እነዲገኝ የፈለገው ነገር ይገኛል እንዲገኝ ያፈለገው ደግሞ አይገኝም

8. አል ኢልም፡- አሏህ ሁሉን ነገር ያውቃል

9. አስሰምእ፡- አሏህ የሚሰሙ ነገራቶችን ባጠቃላይ ይሰማል መስማቱ ግነ በጆሮ አይደለም

10. አል በሶር፡- አሏህ ሊታዮ የሚችሉ ነገራቶችን ሁሉ ያለ አይን ያያል

11. አል ሀያት ፡- አሏህ ህያው ነው ህያውነቱ እንደ ፍጡራን በስጋ በአጥንት ፤ነፍስ፤ በመቅኔነሃ በመሳሰሉ ነገራቶች የተገነባ አይደለም

12. አልከላም፡- አሏህ ይናራል ንግግሩ ንግግሩ ግን እንደ ሰዎች በድምፅ፤ በቋንቋ፤በፊደል እንዲሁም በምላስና በተለያዩ መሳሪያዎች አይደለም።

13. አልሙኻለፈቱ ሊልሀዊስ ፡-አሏህ የፈጠራቸውን ፍጡራች በምንም አይነት መልኩ አይመስልም እርሱ ልክ እንደብናኝ ትንሽ አካልም እንደ አርሽ ግዙፍ አካ አይደለም። ከአርሽ የበለጠ ግዙፍ ነውም አይባልም። እርሱ እንደ ሰው፤ እፅዋት፤ ድንጋይ፤በእጅ የሚዳሰስም ሆነ በእጅ የማይዳሰስ አካል አይደለም።

እንደዛውም አካላት በሚገለፁባቸው ባህሪያት ማለትም እንደ ምላስ እንደ ቅርፅ እንደ ቀለም እንደ እንቅስቃሴና መረጋጋት ባሉ ባህሪያት አይገለፅም። ወይም አሏ ቦታ ይይዛል አቅጣጫን ይቅጣጫል አይባልም። ይልቁንስ አሏህ ያለ ቦታ ያለ ጌታ ነው። ባርያ ያሻውን ያህል በአእምሮ ቢያስብና ቢንሰላሰል የአሏህን እውነታ ሊደርስበት አይችልም፡ አሏህም በቁርአን በሱረት ሹራ አንቀፅ /11 ላይ እንዲህ ይላል።.....

ትርጉሙ፡- ‹‹አሏህን የሚመስል ነገር የለም›

የጠሀራ ምእራፍ

ክፍል የውዱእ ግዴዎች ሰድሰት ናቸው:

1ኛ ፊትን ውሀ ሲያስነኩ ለሰላት ጠሀራ መነየት ማሰብ

2ኛ ፊትን ሙሉ በሙሉ ማጠብ ይህም በቁመት ከፀጉር መብቀያ እስከ አገጭ በወርድ ከጆሮ በር እስከ ጆሮ በር ማለት ነው።

3ኛ ሁለት እጆችን እስከ ክርን (ከክርን ጋር) ማጠብ

4ኛ የተወነውን የራስ (ጭንቅላት) ክፍል ማበስ

5ኛ ሁለቱን እግሮች ከነቁርጭምጭሚቱ ማጠብ

6ኛ ቅደም ተከተሉን መጠበቅ

ክፍል ውዱእ የሚያበላሹ ነገራቶች:

1ኛ ከሁለቱ ቆሻሻ ማስወገጃ በአንዱ የወጣ ነገር መንይ (የዘር ፈሳሽ) እስካልሆነ ድረስ

2ኛ የሰውን ልጅ ብልት ወይንመ የሰገራ መውጫን ቀዳዳ በውስጠኛው መዳፍ ያለ ግርዶሽ መንካት

3ኛ የምትከጀልና ባዳ የሆነችን ሴት ሰውነት ያለ ግርዶሽ መንካት

4ኛ ራስን መሳት ግን አቀማመጡን አስተካሎ የተኛ ሰው ውድእ አይበላሽም

ክፍል ከሁለቱ ቆሻሻ ማስወገጃ የወጣ ማንኛውም እርጥብ ነገር መንይ (የዘር ፈሳሽ) እስካልሆነ ድረስ እስቲንጃእን ያስገድዳል። እስቲንጃውም የሚሆነው ቦታው እስኪጠራ ድረስ በውሀ በማጠብ ወይንም በሶስት ማበስ ወይም ከዛ በላይ ማበስ ቦታ እስኪፀዳ ድረስ ምንም እንኳን ቦታ ላይ ምልክት ቢቀርም ማበስ ተቀባይነት አለው። እበሳውም የሚሆነው ማንሳት በሚችል ንፁህ ደረቅና ክብር በሌለው ነገር ነው። ለምሳሌ እንደ ድንጋይ ፤ቅጠል ይህ ነገር ውሀ እያለም ቢሆን ይሆናል።

ክፍል ሙሉ ትጥበትን የሚያስገድዱ ነገራቶች 5 ናቸው

እነርሱም :-1ኛ ጀናባ እሱም የዘር ፈሳሽ በማውጣት ሲሆን .....ቀባቶች ነገራች መካከል ሲወጣ በሐይል መቆራርጡ በሚወጣበት ግዜ የደስታ ስሜት ማሳየቱ በእርጥበቱ ግዜ የሊጥ ሽታ መሽተቱ በደረቀ ጊዜ ደግሞ የዕንቁላልን ነጩን ክፍል አይነት ሽታ መሽተቱ ይገኝበታል፡

2ኛ ግብረ ስጋ ግንነኙነት እሱም የወንዱ ብልት ክርክራቱ በሴቶ ብልት ውስጥ መግባቲ ነው በሰገራ መውጫ በኩል ቢሆን

3ኛ የወር አበባ እሱም ሴት ልጅ ጤነኛ በሆነችበት ሁኔታ ከማህፀኗ የሚወጣ ደም ነው ትንሹ ጊዜውም አንድ ቀንና አንድ ሌሊት (24 ሰአት) ሲሆን ረጅም ጊዜውም አስራ አምስት ቀንና ሌሊት (15 ቀን)ነው።

4ኛ ኒፋስ እርሱም ሴትልጅ ከወለደች በሆላ ከማህፀኗ የሚወጣ ደም ሲሆን ትንሹ የምራቅ ትፍታ ያክል ነው ብዙ ደግሞ 60 ቀን ይቆያል ። እጥበቱም ግዴታ የሞሆነው ደሙ ሲቋርጥ ነው።

5ኛ መውለድ

<u>ክፍል የትጥበት ግዴታዎች 2 ናቸው</u>

እነሱም :-

1. ንያ ማረግ (ውሀ የመጀመሪያ የሰውነት ክፍል በሚነካበት ጊዜ ትለቁን ሀደስ ማሳን መታጠብን የግድ የሚያደርገውን ነገር ማንሳትን መነየት)
2. ሁሉንም የሰውነት ክፍል ጥቅጥቅ ያለ ፀጉርም ጨምሮ በውሀ አዳርሶ ማጠብ

<u>ክፍል የውዱእ እና የትጥበት ቅድመ ሁኔታዎች 5 ናቸው</u>

እነርሱም:-

1 ሙስሊም

2 መለየት የአዕምሮ ጤነኛ መሆኑና ልጁ ደግሞ የሚነገረውን ንግግር ተረድቶ መልስ መመለስ የሚችል መሆኑ

3 ውሀን ወደ ሰውነት እንዳይደርስ የሚከለክሉ ነገራቶችን ማስወገድ ለምሳሌ:- ጥፍር ቀለም

4 መፍሰስ ማለትም ውሀው የሰውነት ክፍላችን ላይ በባህሪው መፍሰስ ይኖርበታል

5 ውሀው ንፁህ እና ሌላውን ማንፃት የሚችል መሆን አለበት:

ንፁህ ውሀ ሆኖ ሌላውን ማፅዳት የሚችል ፈሳሽ ለውዱእ እና ለእጥበት አይበቃም ለምሳሌ:- እጥበት የተፈፀመበት ውሀ በተለያዮ ንፁህ በሆነ ነገር የተቀየረ እንዲሁም በተነጀሰ ውሀ ማረግ አይችልም ፡

ክፍል ውዱእ የጠበላሸበት ሰው 4 ነገራች ሀራም ይሆኑበታል

1. ሶላት
2. ጠዋፍ (ካእባን መዞር

3. ቁርአንን መሸከም

4. ቁርአንን መንካት

ጀናባ የሆነ ሰው (የዘር ፈሳሽ የፈሰሰው ሰው)ከላይ የተጠቀሱት 4ቱ እና በተጨማሪ

2 ነገራቶች ሀራም ይሆንበታል

1. ቁርአንን መቅራት

2. መስጂድ ውስጥ መቆየት

የወር አበባ(ሀይድ) እና የወሊድ ደም (ኒፋስ) ያለች ሴት ከላይ የተጠቀሱት 6ቱ እና በተጨማሪ 2 ነገራች ሀራም ይሆንታ

1. ደሟ ከመቆሙ በፊት መፆም

2. ከመታጠቦ በፊት ያለግርዶሽ ከእንብርቷ እስከ ጉልበቷ ያለውን የሰውነቷን ክፍል ለባሏ ማመቻቸት

<u>ክፍል፡- ተይሙም እንዲፈቀድ የሚያደርጉ 3 ናቸው</u>

1. ውሀን መፈለጉ ግዴታ የሚሆንት ክልል ውስጥ ፈል ማጣት

2. ውሀን ለጥም ጊዜ መፈለግ

3. ውሀን መጠቀም የሚጎዳው አደጋ ላይ የሚጥል

ክፍል

በማንኛውም ተጠያቂ በሆነ ሙስሊም ላይ እስልምናውን ከሚያበላሽበት ነገር መጠበቅ ግዴታው ነው እስልምናውን የሚያበላሽበት ነገር ደግሞ ሪዳ ነው አሏህ ይጠብቀንናሪዳ በ3 ይከፈላል እነርሱም

1. የእምነት ሪዳ ቦታውም ልብ ነው

2. የድርጊት ሪዳ ቦታውም በክፍለአካላቶች ነው

3. የንግግር ሪዳ ቦታውም ምላስ ነው

ከእምነት ሪዳዎች መሀከል፡ በአሏህ መኖር መጠራጠር፣በመልእክተኛው መልእክተኝነት መጠራጠር፣በመልእክተኛው እውነተኝነት መጠራጠር፣ በእስልምና ትክክለኛ ሀይማኖትነት መጠራጠር፣በጀነትና በእሳት መኖር መጠራጠር፣በአሏህ(ዋጂብ) በሆኑ ባህሪቶች መካከል በአንዱ መጠራጠር ለምሳሌ አዋቂ መሆኑ፣ቻይ መሆኑ፣ሰሚ መሆኑን፣ተመልካች መሆኑን፣አሏህ ከፍጥረቶቹ አንዱን ይመስላል ብሎ ማመን ለምሳሌ፡ ሰውን፣ብርሀንን፣አየርን፣ሩህን፣ወይም ምስል አለው፣ቀለም አለው ብሎ ማመንን፣እንዲሁም አሏህን የሚንቀሳቀስ ወይም የሚረጋጋ ነው ብሎ ማመን፣አሏህን በቦታና በአቅጣጫ መግለጽ፣ከአሏህ ጋር እንደርሱ ለመኖሩ መጀመርያ የሌለው

ቀዳማዊ የሆነን ነገር ከፍጥረታት ውስጥ አለ ብሎ ማመን፣መውሳኔ ማስዋሸት ማለትም ማንኛውም አካልም ሆነ ድርጊት ያለ አሏህ ውሳኔና ፈጣሪነት ተገኘ ብሎ ማመን፣ በኢስላም ኡለማኦች ዘንድ ሀራምነቱ ስምምነት ያገኘችና በሰዎች መካከልም ሀጥያትነቱ ግልጽ የሆነ ነገር ሀላል ብሎ ማመን ለምሳሌ ዝሙትን፣ስርቆትና፣የመሳሰሉት ነገራቶች እንዲሁም ሀላልነታቸው ግልጽ የሆነ ነገራቶች ሀራም ነው ማለት ከምሳሌ ንግድና ጋብቻ፣ በተጨማሪም ግዴታነታቸው በኡለማኦችዘንድ ስምምነት ያገኘን ነገር ግዴታነቱን መካድ ምሳሌ፡ አምስት ወቅት ሶሏት ወይም በኢስላም ሊቃውንቶች ዘንድ ግዴታነቱን ተቀባይነት የሌለውን ነገር ግዴታ ነው ብሎ ማመን፣ለወደፊቱ ከእስልምና መውጣትን ማሰብ ወይም ልውጣ ወይሥ አልውጣ እያሉ ማወላውል እነኚህ ነገራቶች ወድያውኑ ከእስልምና ያስወጣሉ እንዲሁም የአንድን ነብይ ነብይነት መካድ ካልሆነም በነብያቶች ላይ የማይገቡ ባህርያቶችን መለጠፍ ፣ የአንድን መልእክተኛ ረሱልነት ኡለማኦች እስከተስማሙበት ድረስ ረሱልነትን መካድ አደምንና ኢሳን እንደመሰሉ ረሱሎች ማለት ነው ወይም ከነብዩ ሙሀመድ በኋላ ሌላ ነብይ ይመጣል ብሎ ማመን ከእምነት ሪዳዎች ጥቂቶቹ ናቸው

ከድርጊት ሪዳዎች መሀከል፡ ለጸሀይ ወይም ለጣዎት እንደ መስገድ፣ለሰውልጅ የአምልኮ ሱጁድን መውረድ፣ቁርአንን ቆሻሻ ቦታ ላይ መወርወርወይም በላዩ ላይ የቁርአን አንቀጽ፣ የሸሪአ ድንጋጌዎች እንዲሁም የአላህ ስም የታተመበት (የተጻፈበት) ወረቀት በላዩ ላይ የአላህ ስም መኖሩን እያወቁ ቆሻሻ ላይ መጣል ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው

ከንግግር ሪዳዎች መሀከል፡አላህን መሳደብ፣መቃወምበተላበሰ መልስ ‹አላህ ለምን እንዲህ ያደርጋል›ማለት ወይም ‹አላህ በደለኝ ማለት› እንዲሁም ‹ አላህ ከሰማይ ቢወርድ ራሱ እገኔን ከኔ ማንም አያስጥለውም› ብሎ መናገር ወይም ‹እገሊትን ወንድ አድርጎ ሊፈጥራት ብሎ ሴት ሆነችበት› እንደ ማለት፣ እንደዛውም ማንኛውም እስልምና ሀይማኖትን ወይም የእስልምና መገለጫዎች (ሶላት፣ጾም፣ሀጅ፣ አዛን፣መስጂድ፣ቁርአንና ሌሎችን) የሚያንቋሸሹ ንግግሮች እንዲሁም መልእክተኞችን፣መላእኮችን ጅብሪልንና ሚካኢልን የመሳሰሉትን የሚያንቋሸሹ ንግግሮች፣ በተጨማሪም አላህ ለሙእሚኖች በአኺራ ቃል በገባላቸው ነገራቶች ማንቋሸሽ ለምሳሌ ‹ከጀነት ጸጋ የዱንያ ጸጋ ይሻላል› ማለት እንዲሁም አላህ በካፊሮች ላይ በዛተው ዛቻ (ቅጣት) ማሾፍ ለምሳሌ በኼራ በጀሀንም እሳት እንሞቃለን ብሎ መናገር ሲሆን ከዚህም ባሻገር አንድ ሙስሊም አንተ ካፊር ማለት ይህም በዚህ ንግግር ይህ ሙስሊም ያለበት ሀይማኖት ኩፍር ነው ማለትን ከተፈለገበት ነው ነገር ግን አንተ ካፊር ሲል በውስጡ ያ ሙስሊም ከሚሰራቸው አፀያፊ ስራዎች አንፃር ካፊር ትመስላልህ ማለትን ፈልጎበት ከሆነ ኩፍር (ሪዳ) አይሆንም ከሀራም ግን አይፀዳም።

ወይም አንድ ከእስልምና ውጭ የሆነ ሰው ሲሞት አሏህ ይማረው ወይም ወንጀሉን ይማርለት ብሎ ዱአ ማድረግ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው

ክፍል፡-

አንድ ሰው የሪዳን ንግግር ትርጉሙን እስካላወቀ ድረስ ከተናገረ የንግግሩን ፍርድ (ብያኔ) ቢያውቅም ባያውቅም በንግግሩ ከእስልምና መውጣትን ቢስብም ባያስብም ንግግሩ የምሩን ቢሆንም እየቀለደ ወይም በንዴት ወቅት የተናገረው ቃል ቢምንበትም ባያምንበትም ከእስልምና ይወጣል ።

ለምሳሌ አንድ ሰው ለሌላኛው አንተ የአሏህ ልጅ ካለው ተጋሪው አሏህ ልጅ የለውም ብ ቢያምን እንኳን ፣ኮእስልምና ይወጣል። ይህንንም የምንረዳው ከመልእክተኛው ሶለሏሁ አለይሂ ወሰለም ንግግር ነው፡- የአሏህ መልእክተኛ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹አንድ ባሪያ አንድ ንግግር ይናገራል ይህች ንግግርም ምትጎዳው አይመስለውም ነገር ግን በሷ ሰበብ በጀሀነም ጉድጓድ ሰባ አመት ይሸቆለቆላል›› ቲርሚዝይ ዘግበው ሀሰን ነው ብለውታል።

ክፍል፡-

ከእስልምና በሪዳ ምክኒያት የወጣ ሰው ወዲያውኑ ወደ እስልምና ሁለቱን የምስክር ሀረጎች በአንደበቱ በመመስከር መመለስ ይገደዳል። ሁለቱ የምስክር ሀረጎችም አሸሀዱ አን ላኢላሀ ኢለሏህ ወ አሸሀዱ በአነ ሙሀመደ ረሱሉሏህ ናቸው። ይህንን ከአረብኛ ቋንቋ ውጪ በሆነ ቋንቋ ማትለትም ይቻላል። እንዲሁም ከእስልምና ለመውጣቱ ምክንያት የሆነውን ነገርም ሊተወው ይገባል። ወደ እስልምና ከመመለሱም በተጨማሪ በእርሱ ላይ በተከሰተበት ነገር ሊፀፀት ይገባል።እናም ወደ ፊት ወደዚያ ነገር ላለመመለስ መቁረጥ አለበት።

ክፍል:-

ከሪዳ ህግጋት መካከል ሙርተድ (ከእስልምና በሪዳ የወጣ ሰው) ፆሙ ይበላሻል፤ቴሙሙ ይበላሻል፤ጋብቻው ከግንኙነት በፊት ከሆነ ይበላሻል፤ እንዲሁም ከግንኙነት በኋላ ከሆነ በኢዳ (የመቆያ ጊዜ) ወቅት ካልተመለሰ ይበላሻል ኢዳ ማለት የወር አበባ ለምታይ ሴት (3 ግዜ የወር አበባ አይታ ስትጸዳ) የወር አበባ ለማታይ ሴት ደግሞ (3 ወራት) እርጉዝ ለሆነች ሴት ደግሞ እስክትወልድ ድረስ ነው።

ሙርተድ (በሪዳ ምክንያት ከእስልምና የወጣ)ከሱ ጋር ጋብቻ ማድረግ አይበቃም እንደሱ ሙርተድ የሆነችውንም ማግባት አይችልም፣እሱ ያረደውም በክት ነው ፣አይወርስም፣አይወረስምም፣ሲሞት ጥሎት ያለፈው ንብረቱ ለሙስሊሞች ጥቅም ይውላል፣በሱ ላይ ሲሞት መስገድም አይበቃም ማጠቡም ይሁን መገነዙ ግዴታ አይሆንምበሙስሊሞች መቃብር ውስጥም መቅበር አይቻልም

የጦሀራ ምእራፍ

የውዱእ ግዴታዎች 6 ናቸው እነርሱም:-

1. ፊትን ውሃ ሲያስነኩ ለሶላት ጦሀራ መነየት (ማሰብ
2. ፊትን ሙሉ በሙሉ ማጠብ ይህም በቁመት ከጸጉር መብቀያ እስከ አገጭ በወርድ ከጆሮ በር እስከ ጆሮ በር ማለት ነው
3. ሁለት እጆችን እስከ ክርን (ከክርን ጋር)ድረስ ማጠብ
4. የተወሰነውን የራስ (ጭንቅላት) ክፍል ማበስ
5. ሁለቱን እግሮች ከነቁርጭምጭሚቱ ማጠብ
6. ቅደም ተከተሉን መጠበቅ

ክፍል

ውዱእን የሚያበላሹ ነገሮች

1. ከሁለቱ ቆሻሻ ማስወገጃዎች በአንዱ የወጣ ነገር መንይ (የዘር ፈሳሽ) እስካሆነ ድረስ

2. የሰውን ልጅ ብልት ወይንም የሰገራ መውጫን ቀዳዳ በውስጠኛው መዳፍ ያለ ግርዶሽ መንካት
3. የምትከጀልና ባዳ (አጅነብይ ሴት) የሆነችን ሴት ሰውነት ያለ ግርዶሽ መንካት
4. ራስን መሳት ግን አቀማመጡን አስተካክሎ የተኛ ሰው ውዱእ አይበላሽበትም

ክፍል

ከሁለቱ ቆሻሻ ማስወገጃ የወጣ ማንኛውም እርጥብ ነገር መንይ (የዘር ፈሳሽ) እስካሆነ ድረስ እስቲንጃ ያስገድዳል እስቲንጃውም የሚሆነው ቦታው እስኪጠራ ድረስ በውሀ በማጠብ ወይም በሶስት ማበስ ወይም ከዛ በላይ በሆነ ማበስ ቦታው እስኪጸዳ ድረስ ምንም እንኳን ቦታው ላይ ምልክት ቢቀርም ማበስ ተቀባይነት አለው::ማበስ የሚሆነውም ማንሳት የሚችል፣ንጹህ፣ደረቅና፣ክብር በሌለው ነገር ነው ለምሳሌ፡-እንደ ድንጋይ፣ ቅጠል፣ይህይህ ነገር ውሀም እያለም ቢሆን ይሆናል::

ክፍል

ሙሉ ትጥበት የሚያስገድዱ ነገራቶች 5 ናቸው እነርሱም፡-

1. ጀናባ፡- እርሱም የዘር ፈሳሽ በማውጣት ሲሆን (የዘር ፈሳሹ) ከሚታወቅባቸው ነገራቶች መካከል ሲወጣ በሀይል፣መቆራረጡ፣በሚወጣበት ግዜ የደስታ ስሜት መሰማቱ፣በእርጥበቱ ግዜ የሊጥ ሽታ መሽተቱ በደረቁ ግዜ ደግሞ እንቁላልን ነጩን ክፍል አይነት ሽታ መሽተቱ ይገኝበታል::
2. የግብረ ስጋ ግንኙነት፡- እርሱም የወንዱ ብልት (ክርክር) በሴቷ ብልት ውስጥ መግባቱ ነው በሰገራ መውጫም በኩልም ቢሆን
3. የወር አበባ ደም፡-ሴት ልጅ ጤነኛ በሆነችበት ሆኔታ ከማህጸኗ የሚወጣ ደም ነው፡፤ትንሹ ግዜውም አንድ ቀንና አንድ ለሊት (24 ሰአት) ሲሆን ረጅም ግዜውም አስራ አምስት ቀንና ለሊት (15 ቀን) ነው
4. ኒፋስ፡- እርሱም ሴት ልጅ ከወለደች በኃላ ከማህጸኗ የሚወጣ ደም ሲሆን ትንሹ የምራቅ ትፍታ ያክል ነው ብዙው ደግሞ 60 ቀን ነው
5. መውለድ

ክፍል

የትጥበት ግዴታዎች 2 ናቸው እርሱም፡-

1) ኒያ ማድረግ፡-(ውሀ የመጀመርያው የሰውነት ክፍል በሚነካበት ግዜ ትልቁን ሀደስ ማንሳትን ትጥበትን መታጠብን የግድ የሚያደርገውን ነር ማንሳትን መነየት
2) ሁሉንም የሰውነት ክፍል ጥቅጥቅ ያለ ጸጉርን ጨምሮ በውሀ አዳርሶ ማጠብ

ክፍል

የውዱእ እና የትጥበት ቅድመ ሁኔታዎች 5 ናቸው እነርሱም፡-

1) ሙስሊም መሆን
2) መለየት (አእምሮ ጤነኛ መሆኑና ልጅ ደግሞ የሚናገረውን ንግግር ገብቶት መልስ መመለስ የሚችል መሆኑ)
3) ውሀን ወደ ሰውነት እንዳይደርስ የሚከለክሉ ነገራቶች ማስወገድ ለምሳሌ፡-ጥፍር ቀለም
4) መፍሰስ ፡- ማለትም ውሀው የሰውነት ክፍላችን ላይ በባህሪው መፍሰስ ይኖርበታል
5) ውሀው ንጹህ እና ሌላውን ማጽዳት የሚችል መሆን አለበት

- ንጹህ ውሀ ሆኖ ሌላውን ማጽዳት የማይችል ፈሳሽ ለውዱእ እና ለትጥበት አይበቃም ለምሳሌ ፤- ትጥበት የተፈጸመበት ውሀ፣ በተለያዩ ንጹህ በሆነ ነገር የተቀየረ እንዲሁም በተነጀሰ ውሀ ማድረግ አይቻልም

ክፍል

ውዱእ የተበላሸበት ሰው 4 ነገራቶች ሃራም ይሆኑበታል እነርሱም፡-

1. ሷኋት
2. ጠዋፍ (ካእባን መዞር)
3. ቁርአን መሸከም
4. ቁርአንን መንካት

➢ ጀናባ የሆነ ሰው (የዘር ፈሳሽ የፈሰሰው ሰው)ከላይ የተጠቀሱት 4ቱ እና በተጨማሪ 2 ነገራቶች ሃራም ይሆኑበታል

1. ቁርአንን መንካት
2. መስጂድ ውስጥ መቀመጥ

➢ የወር አበባ (ሀይድ) እና የወሊድ ደም (ኒፋስ) ላይ ያለች ሴት ከላይ የተጠቀሱት 6ቱ እና በተጨማሪ 2ት ነገራቶች ሀራም ይሆኑባታል

1) ደሟ ከመቆሙ በፊት መጾም
2) ከመታጠቧ በፊት ያለ ግርዶሽ ከእንብርቷ እስከ ጉልበቷ ያለውን የሰውነቷን ክፍል ለባሏ ማመቻቸት

ክፍል

ተየሙም እንዲፈቀድ የሚደርጉ ነገራቶች 3 ናቸው

1. ውሀን መፈለጉ ግዴታ የሚሆንበት ክልል ውስጥ ፈልጎ ማጣት
2. ውሀን ለጥም ግዜ መፈለግ
3. ውሀን መጠቀም የሚጎዳው (አደጋ ላይ የሚጥል)

ክፍል

የተየሙም ቅድመ ሁኔታዎች 4 ናቸው፡-

1) ጥርት ያለ ንጹህ የሆነ ውሀ (ጧሀራ የሆነ) ከዚህ በፊት ተየሙም ያልተደረገበት አፈር መሆን አለበት
2) አፈሩን 2 ግዜ ወይም ከ2 ግዜ በላይ በመምታት የተነሳ መሆን ይኖርበታል
3) ተየሙሙ የሶላት ወቅት ከገባ በኃላ ሊሆን የግድ ነው

ክፍል

የተየሙም ግዴታዎች 4 ናቸው እነርሱም፡-

1) አፈርን ከመሬት አንስቶ ወደ ፊቱ እስከሚያደርስ ድረስ ግዴታ የሆነውን ሶላት እንዲፈቀድለት የሚያስችል ንያ መነየት
2) ፊትን ማበስ
3) ሁለት እጆችን እስከ ክንድ ድረስ ማበስ
4) ቅደም ተከተል መጠበቅ

ክፍል፡- እንደ ሽንት፣ሰገራ፣ደም መሳሰሉትን ነጃሳዎች ማስወገድ ግዴታ ነው።ይህ የሚሆነው የነጃሳውን አካል እና ባህሪያቶች በማጥፋት ነው ለምሳሌ ጣእሙን ፣ቀለሙን ወይም ሽታውን ማንጻት በሚችል ውሀ በማስወገድ ነው። ነጃሳው የሚታይ ካልሆነ አንድ ግዜ በላዩ ላይ ውሀ ማፍሰስ በቂ ነው።ለምሳሌ ጣእም፣ሽታው፣ቀለም የሌለው የደረቀ ሽንት

የውሀ ወይም የአሳማ ነጃሳ ከሆነ ግን ነጃሳው ያረፈበት ቦታ በተከታታይ ለ7 ግዜ ማጠብ ከ7 ት አንዱ ደግሞ በንጹህ አፈር በተቀላቀለ ሊሆን ይገባል የነጃሳው አካልና ባህሪቶቹ እስኪጠፋ ድረስ የሚደረገው እጥበት ቁጥሩ ቢበዛም እንደ አንድ ይቆጠራል።ማንኛውም አይነት ነጃሳ በሚጸዳበት ግዜ ነጃሳው ውሀ ውስጥ መግባት ሳይሆን ውሀ በላዩ ላይ ማፍሰስ ግድ ነው፡፤ይህም ውሀው ትንሽ ከሆነ ነው

የሶላት ምእራፍ

ክፍል

ዋጂብ (ግዴታ)ከሆኑ ነገራቶች መካከል በቀንና በለሊት(በ24 ሰአት) የሚሰገዱ ሶላቶች 5 ናቸው ይገኙበታል

1. ዝሁር፡- 4 ረከአ ሲሆን ወቅቱ የሚገባው ጸሀይ ከመሀል ሰማይ ወደ ምእራብ ስታጋድል ነው።።ወቅቱም የሁሉም ነገር ጥላ ከነገሩ ቁመቱ ጋር እኩል ሆኖ ዚሉል ኢስቲዋ (እኩለ ቀን ላይ በማንኛውም ነገር ላይ የሚታይ ጥላ) እስኪጨመርበት የሚሆነው ግዜ ድረስ ይቆያል

2. አስር፡-አራት ረከአ ሲሆን ወቅቱ የሚገባው ልክ የዝሁር ወቅት ሲወጣ ሲሆን የሚወጣውም ጸሀይ ስትጠልቅ ነው

3. መግሪብ፡-ሶስት ረከአ ሲሆን ወቅቱ የሚገባው ልክ የአስር ወቅት ሲወጣ (ጸሀይ ስትገባ) ይሀንና የሚወጣውም ቀዩ ወጋገን ሲጠፋ ነው።። እሱም የጸሀይን መግባት ተከትሎ በጸሀይ መግቢያ በኩል ብርሀን ነው

4. ኢሻእ፡-አራት ረከአ ሲሆን ወቅቱም ወቅቱም የመግሪብ ወቅት እንደወጣ ይጀምርና እውነተኛው ጎህ ሲቀድ ይወጣል

5. ሱብሂ፡-ሁለት ረከአ ሲሆን ወቅቱም የኢሻ ሶላት ወቅት መውጣትን ተከትሎ ይገባና ልክ ጸሀይ ስትወጣ ያልቃል

ክፍል፡-

የወር አበባ ላይ ወይም የወሊደ ደም ላይ ካለች ሴት ውጪ ያሉ ማንኛውም ለአካ መጠን የደረሰ አእምሮው ጤነኛ የሆነ ሙስሊም እነኚህን ከላይ የተዘረዘሩትን 5 ወቅት ሶላቶች መስገድ ይገደዳል።።እንዲሁም እነኚህን ሶላቶች ከግዜያቸው አስቀድሞ ወይም አዘግይቶ (አሳልፎ) መስገድ ሀራም ነው።።ነገር ግን መንገደኛ እንደሆነ ሰው ተቀባይነት ሰበብ ያላቸው ሰዎች ከዚህ ፍርድ አይካተቱም።።እነኚህን ሰላቶች እያወቁ ከግዜያቸው ያሳለፈ ሰው ትልቅ የሆነ ወንጀል ላይ ይወድቃል ምትኩንም(ቀዷውንም) ወድያው መስገድ ይኖርበታል።። ነገር ግን ተኝቶ ወይም ረስቶ ወቅቱን ያሳለፈ ሰው ባስታወሰ ግዜ ሶላቱን መስገድ ይኖርበታል ግን ምንም አይነት ወንጀል ላይ አይወድቅም

ክፍል

በማንኛውም የለዩ (7አመት የሞላቸው)ልጆች አሳዳጊ ታዳጊው ሰባት(7) አመት ሲሞላው በሶላት ማዘዝ ግዴታ ይሆንበታል።።እንዲሁም ታዳጊው አስር አመት(10) ሞልቶት ሶላት ካልሰገደ የመግረፍ(እንዲሰግድ ማድረግ) ግዴታ ይኖርበታል በተጨማሪም ታዳጊዎቹ የአቂዳን፣የአህካምን (ህግጋትን) እንዲሁም ይሄ

ሃራም ነው ይሄ ሃላል ነው የሚሉትን ነገራቶች ማስተማር ግዴታ ነው።በተጓዳኝም በማንኛውም ሙስሊም ላይ ሚስቱንና ሊታዘዙት የሚችሉትን ሰዎችን አቂዳና የሸሪአውን ህግጋት በማስተማር በሶላት ማዘዝ ግዴታ ይኖርበታል።

ክፍል

ሶላት ትክክል እንዲሆን የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎች ዘጠኝ ናቸው እነርሱም፡-

1. ከትልቁም ይሁን ከትንሹ ትጥበትን ግዴታ ከሚያደርጉ ነገራት መጽዳት
2. ከሰውነቱ፣ከልብሱና ሰውነቱን የሚያገኘው ቦታ ከነጃሳ መጽዳት
3. ቂብላን መቀጣጨት
4. የሶላት ወቅት መግባት
5. ሙስሊም መሆን
6. መለየት መቻል (መቻል ማለትም የአእምሮ ጤነኝነትና ልጁ ደግሞ የሚለይበት ግዜ ላይ መድረሱ)
7. የሶላቱን ግዴታነት ማወቁ
8. ግዴታ ከሆኑ ነገራት አንዱን እንኳ ሱና ነው ብሎ አለማመን
9. ሴት ከመዳፏና ከፊትዋ ውጪ ያለውን መላው ሰውነቷን መሸፈን

ክፍል

የሶላት ማእዘናት (ያለነሱ የማይበቃ ነገራቶች) 17 ናቸው እነርሱም፡-

1) ከተክቢራ ጋር አቆራኝቶ በቀልብ ኒያ ማድረግ ለምሳሌ፡-ግዴታ የሆነውን የአስርን ሶላት እሰግዳለሁ ማለት
2) (አሏሁ አክበር)ማለት
3) ለሚችል ሰው በፈርድ (ግዴታ) ሶላት ላይ መቆም
4) የፋቲሀን ምእራፍ በትክክል ማንበብ
5) ሩኩእ ማድረግ ማለትም መዳፎቹ ጉልበቱን መንካት የሚችሉበት ደረጃ ድረስ ከወገብ ማጎንበስ
6) በመረጋጋት ባጎነበስንበት ቅጽበት ለተወሰነ ግዜ መላው ሰውነቱን ከእንቅስቃሴ መግታት

7) መመለስ ማለትም ካጎነበሰ በኃላ ከዚያ በፊት ወደነበረበት መመለስ

8) በሱ ላይ መረጋጋት

9) 2 ሱጁዶችን መውረድ እርሱም የሚሆነው ግንባሩን

10) በዚህ ላይ መረጋጋት

11)በሁለቱ ሱጁዶች መካከል መቀመጥ

12)በሱ ላይ መረጋጋት

13)ለመጨረሻው ተሸሁድ መቀመጥ

14)የመጨረሻው ተሸሁድ ሙሉ ቃላቱም ይህ ነው ፡- አተትህያቱ አልሙበረካቱ አስሶለዋቱ አጥጦይባቱ ሊላህ አሰላሙ አለይክ አዩሃን ነብዩ ወራህመቱሏሂ ወበረካቱህ አሰላሙ አለይና ወአላ ኢባዲላሂ አሷሊሂን አሸሀዱ አን ላ ኢላሀ ኢለሏህ ወአነ ሙሀመደን ረሱሉሏህ

15)በመልእክተኛው ላይ ሶለዋት ማወረድ ሙሉ ንባቡም አሏሁመ ሰሊ አላ ሙሀመድ ወአላ አሊ ሙሀመድ ከማ ሶለይተ አላ ኢብራሂም ወባሪክ አላ ሙሀመድ መአላ አሊ ሙሀመድ ከማ ባረክተ አላ ኢብራሂም ወአላ አሊ ኢብራሂም ኢነከ ሀሚዱን መጂድ ነው

16)ሰላምታ ይህም ‹አሰላሙ አለይኩም ›በማለት ነው

17)ቅደም ተከተሉን መጠበቅ አንድ ሰው እያወቀ ከሩኩኡ በፊት ሱጁድ ካደረገ ሶላቱ ይበላሻል

ክፍል

ሶላትን የሚያበላሹ ነገራቶች 15 ናቸው እነርሱም

1. ትልቁን ወይም ትንሹን ትጥበትን የሚያስገድድ ነገር ሲከሰት
2. ነጃሳ በሰውነቱ ወይም በልብስ ላይ ካረፈና ወድያውኑ ካለምንም ሸክም አንጥረው እስካላስወገዱ ድረስ
3. የሀፍረተ ገላ መገለጥ
4. ከቂብላ አቅጣጫ ደረትን ማዞር
5. ሁለት ፊደል ወይም ትርጉም ያለው አንድን ፊደል እያወቁ መናገር
6. ከትከት ብሎ መሳቅ ማለትም ድምጽን አውጥቶ መሳቅ
7. ረስቶና ትንሽ እስካሆነ ድረስ እያወቀ መብላት (ትንሽም ቢሆን)

8. ብዙ እንቅስቃሴ ማድረግ ማለትም(ሶስት ተከታታይ እንቅስቃሴዎች)

9. ለጨዋታ ብሎ አንድ እንቅስቃሴም ቢሆን ማድረግ

10. አስቀያሚ እንቅስቃሴ እንደ መዝለል ያለ

11. እያወቁ የድርጊት ማእዘን መጨመር

12. ሲላትን ለማቋረጥ መወሰን

13. ሶላትን መቁረጥ ከሆነ ነገር ላይ ማንጠልጠል

14. ሶላትን ልቁረጥ ወይስ አልቁረጥ ብሎ ማወላወል

15. ሪዳ (እስልምናን መቁረጥ)

ክፍል

የህብረት (የጀመአ ሶላት) ለአካለ መጠን በደረሱና ነጻ በሆኑ ወንዶች እንዲሁም ቋሚ ነዋሪ በሆኑ ሰዎች ላይ የተወሰነ ሰው ከሰራው ከሌላው ላይ የሚነሳ